የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION



# በከረዩ የሚችሌ ገዳ የጅላ አባላት ግድያ ላይ የተደረገ የምርመራ ሪፖርት

*“በመጨረሻም የሚገደሉበት ሰዓት እየደረሰ እንደሆነ ተነገራቸው”*

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# “በመጨረሻም የሚገደሉበት ሰዓት እየደረሰ እንደሆነ ተነገራቸው”

## በከረዩ የሚችሌ ገዳ የጅላ* አባላት ግድያ ላይ የተደረገ

## የምርመራ ሪፖርት

### መግቢያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ፈንታሌ ወረዳ በኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. የከረዩ የሚችሌ ገዳ አባላት አርዳ ጅላ ላይ በተፈጸመ ጥቃት የሕይወትና የአካል ጉዳት ስለመፈጸሙ በደረሰው ጥቆማ መሰረት፣ ከታኅሣሥ 7 እስከ ታኅሣሥ 12 ቀን 2014 ዓ.ም. በቦታው በመገኘት ምርመራ አካሂዷል።

የመርማሪ ቡድኑ ምርመራውን ለማከናወን የአይን ምስክሮችን፣ተጎጂዎችን፣ የተጎጂ ቤተሰቦችን እና የከረዩ ማኅበረሰብ የሀገር ሽማግሌዎችን አነጋግሯል። በተጨማሪም ከመንግስት አካላት የፈንታሌ ወረዳ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት (ጽ/ቤት)፣ የዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፣ የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የወረዳው ጸጥታ ጽ/ቤት፣ በዞን ደረጃ ደግሞ ከምሥራቅ ሸዋ ዞን አስተዳደር፣ የሰላምና ፀጥታ ቢሮ እና የፖሊስ መምሪያ በማነጋገር በአጠቃላይ ከ48 ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት አድርጓል፡፡ ተጎጂዎች አንድ ላይ ተሰብስበው ይኖሩበት የነበረ ስፍራ፣ ግድያው ተፈጸመበት የተባለ ቦታ እንዲሁም የሟቾች አስክሬን ያረፈበት የመቃብር ቦታ በመሄድ የመስክ ምልከታ አድርጓል፡፡

### ዳራ

የፈንታሌ ወረዳ በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዱ ሲሆን በደቡብ ምሥራቅ በአርሲ ዞን፣ በደቡብ ምዕራብ በቦሰት ወረዳ፣ በሰሜን ምዕራብ በአማራ ክልል እንዲሁም በሰሜን ምሥራቅ በአፋር ክልል ይዋሰናል፡፡ በወረዳው በተለይም በአማራ እና በአፋር ክልል አዋሳኝ አከባቢዎች በኩል የሕወሃት ኃይሎች ሰርጎ እዳይገቡ እና የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በተለምዶ “ኦነግ ሸኔ” ተብሎ የሚጠራ ታጣቂ ቡድን) በአከባቢው ይንቀሳቀሳል በሚል በአካባቢው መስተዳድር አስተባባሪነት የታጠቁ ቡድኖችን እንቅስቃሴዎች የሚያወግዙ ሰላማዊ ሰልፎች፣ እንዲሁም በፀጥታ ኃይሎች የሚመሩ ልዩ ልዩ “ኦፕሬሽኖች” (የፀጥታ ማስጠበቅ እንቅስቃሴዎች) ይካሄዱ ነበር፡፡

* በከረዩ ማኅበረሰብ የገዳ ሥርዓት መሰረት የሥልጣን ዘመኑ የደረሰ ቡድን አደረጃጀቱን እና አባላቱን ይዞ ለብቻው ተነጥሎ አርዳ ጅላ (የመኖርያ ስፍራ) በመመስረት ለስምንት ዓመታት ከኖረ በኋላ የሥልጣን ዘመኑ ሲጠናቀቅ ለሚቀጥለው የገዳ ቡድን ሥልጣኑን በማስረከብ ከቦታው ይበተናል፡፡

ኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም. ከክልል፣ ከዞን እና ከፈንታሌ ወረዳ የተውጣጡ የፀጥታ አካላት ወደ ፈንታሌ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች በመሄድ ከነዋሪዎች ጋር በአከባቢው ስላለው የፀጥታ ሁኔታ ውይይትና ቅኝት ካደረጉ በኋላ፣ በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት አከባቢ በአራት ፓትሮል መኪና ወደ መተሃራ ከተማ ሲመለሱ በወረዳው ሀሮ ቀርሳ ቀበሌ ልዩ ስሙ ኢፍቱ በተባለ ቦታ ላይ እንደደረሱ ማንነታቸው ያልታወቀ ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት ሳጂን በሻዳ ጎንፋ ፣ሳጂን ዶዮ አለሙ፣ ኢንስፔክተር ፈጠነ ዳርባ፣ ረዳት ሳጂን ደቀባ ድርባ፣ አንፔክተር በዳሶ ድርባ፣ በሽር መሀመድ፣ ዋስሁን ወንድሙ፣ አበራ ደምስ፣ ድንቁ አስፋው፣ ፍቃዱ ኢያና እና ሽሙዲ አህመድ የተባሉ በአጠቃላይ 11 የኦሮሚያ ልዩ ኃይል አባላት በታጣቂዎቹ መገደላቸውና ፣ እንዲሁም በሁለት መደበኛ ፖሊሶች እና ቢያንስ በ7 ሌሎች የፖሊስ አባላት ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን መረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የፀጥታ ኃይሉ ሲንቀሳቀሱባቸው የነበሩ ሦስት የፖሊስ መኪኖች ሙሉ በሙሉ የተቃጠሉ ሲሆን፣ ሁለት የፓትሮል መኪኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን የፖሊስና የአስተዳደር አካላት አስረድተዋል።

ከጥቃቱ በኋላም ታጣቂዎቹ አስክሬን እንዳይነሳ በመከልከላቸው የሟቾች አስክሬን ሌሊቱን ሜዳ ላይ አድሮ እስከ ኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00-4፡00 ሰዓት ድረስ መቆየቱን የአስተዳደርና የፀጥታ አካላት እንዲሁም አንድ ከጥቃቱ የተረፈ የፖሊስ አባል ገልጸዋል። ሁኔታውንም ሲያስረዱ፡

> *"ጥቃት ሲፈጽሙ የነበሩት "የኦነግ ሸኔ" አባላት ሲሆኑ ከመካከላቸው የማውቃቸው የአከባቢው ተወላጆች አሉበት፤ ታጣቂዎቹ በተኮሱት ጥይት ፖሊስ ሲወድቅ እልልታ ያሰሙ ነበር" ብለዋል።*

ከላይ ከተጠቀሰው ጥቃት አስቀድሞም ሌሎች ተመሳሳይ ጥቃቶች በወረዳው በታጠቁ ቡድኖች ይፈጸሙ እንደነበረና ይህንንም ጥቃት ተከትሎ የክልሉ መንግስት የጥቃቱን ፈጻሚዎች ለመያዝ ልዩ ልዩ ኦፐሬሽኖች (የፀጥታ ማስጠበቅ እንቅስቃሴዎች) ሲያካሄድ የነበረ መሆኑን የምርመራ ቡድኑ ከነዋሪዎችና ከላይ ከተዘረዘሩ የአስተዳደር እና የፀጥታ አካላት መገንዘብ ችሏል፡፡

በከረዩ የገዳ ሥርዓት የሥልጣን ተዋረድ መሰረት ከሦስት ዓመታት በፊት ሥልጣን የተረከበው የሚችሌ ቡድን የገዳ አባላት አርዳ ጅላ (የገዳ ሥርዓት የአመራር አባላት የመኖርያ ስፍራ) በፈንታሌ ወረዳ ጡጢቲ ቀበሌ ልዩ ስሙ ዴዲቲ ካራ እና መቱማ በተባሉ ቦታዎች ይገኛል። ይህ አርዳ ጅላ ከአዲስ አበባ-ጂቡቲ የአስፋልት መንገድ በግምት ከ3-5 ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ ሜዳማ በሆነ ስፍራ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የአባ ገዳ አርማ (ፋጂ) ተሰቅሎ ይታያል። የጅላ አባላት ደግሞ በባንድራው ዙሪያ ክብ ክብ ጎጆ ሰርተው ይኖራሉ። በዚህ የመኖርያ ሰፈር 63 የጅላ አባል የሆኑ አባወራዎችና ቤተሰቦቻቸው ይገኙ የነበረ ሲሆን፣ በሥርዓቱ ደንብ መሰረት ከጅላ አባላቱ እና ቤተሰቦቻቸው ውጪ ሌላ በስፍራው የሚኖር ሰው የሌለ መሆኑን የምርመራ ቡድኑ ያነጋገራቸው የጅላ አባላት ቤተሰቦች እና የአከባቢው ማኅበረሰብ አባላት ያስረዳሉ።

## የምርመራው ዋና ዋና ግኝቶች

ኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም በምስራቅ ሸዋ ዞን ፈንታሌ እና ቦሰት ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ቀበሌዎች ውስጥ "የኦነግ ሸኔ" ታጣቂዎች ይንቀሳቀሳሉ ተብሎ ስለሚጠረጠር ከመደበኛ ፖሊስ፣ ከልዩ ኃይል እና ከሚሊሻ የተውጣጡ 400 የሚሆኑ አባላት ለኦፕሬሽን ወደ ወረዳዎቹ ተሰማርተው የነበረ መሆኑን ከፀጥታ አካላት ከተገኘ መረጃ መረዳት ተችሏል። በእለቱ በኦፕሬሽኑ ላይ የነበሩ የፀጥታ አባላት በቦሰት ተራራ አከባቢ የሚገኘውን የከረዩ የሚችሌ ገዳ አርዳ ጅላ ያለበትን አከባቢ ሲያልፉ አባገዳዎችን አነጋግረው እንደነበረና ሲመለሱ ደግሞ "ከኦነግ ሸኔ" ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተጠረጠሩ ሰዎችን ይዘው መመለሳቸውን የአይን እማኞችና የምሥራቅ ሸዋ ዞን አስተዳደር ገልጸዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው፣ ከኦፕሬሽን ሲመለሱ በነበሩ የፖሊስ አባላት ላይ ጥቃት ከተፈጸመ በኋላ "ኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በግምት ከቀኑ 6፡00 ሰዓት አከባቢ ከ100 ያላነሱ የኦሮሚያ ልዩ ኃይልና የመደበኛ ፖሊስ ዩኒፎርም የለበሱ የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች በፖሊስ መኪና መጥተው መኪናዎቻቸውን አስፋልት ዳር በማቆም በእግር የሚችሌ ገዳ አርዳ ጅላ ወደሚገኝበት ሰፈር ደረሱ።" የፖሊስ አባላቱ በቦታው እንደደረሱ ቤት ለቤት በመዞር ጭምር በአካባቢው የነበሩ ወንዶች የጅላ አባላትን አንድ ቦታ ላይ እንደሰበሰቡ፣የያዙትንም የጦር መሳሪያ እንደተቀበሏቸው፣ ቤት ለቤት እየሄዱ በመፈተሽም መሳሪያ፣ ገንዘብ፣ ሞባይል ወዘተ የወሰዱ መሆኑን ነዋሪዎች ለመርማሪ ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

ድርጊቱ ሲፈጸም በቦታው የነበረ አንድ የአይን እማኝ የነበረውን ሁኔታ አንደሚከተለው ለምርመራ ቡድኑ አስረድቷል፡-

> "ሁሉንም በቦታው የነበሩ ወንድ የጅላ አባላትን ሰበሰቡ፣ቤት የቀሩ ሰዎችንም እንዲወጡ አድርገው አንድ ቦታ ሰብስበው አስቀመጧቸው፡፡ የጅላ አባላቱ ለውይይት ወይም ለስብሰባ የተጠሩ ነበር የመሰላቸው። በመቀጠል የጅላ አባላቱ የያዙትን መሳሪያ አንዲያስረክቡ ተደረገ፣ ቤት የቀረውንም ቤቶቻቸውን እየፈተሹ ወሰዱ፡፡የያዙት መሳሪያ ፍቃድ ያለው ነበር፡፡ 'በሀሮ ቀርሳ የተገደሉት ፖሊሶችን ማን ነው የገደላቸው?' እያሉ ደጋግመው እየጠየቁ በተቀመጡበት ቦታ ይዝቱባቸው ነበር፡፡ እነሱም ድርጊቱ ሌላ ቀበሌ ላይ የተፈጸመ በመሆኑ እንደማያውቁ አስረዷቸው።ፖሊሶቹ ግን 'ካልነገራችሁን እንገድላችኋለን' እያሉ ያስፈራሯቸው ነበር፡፡"

በተጨማሪም የፀጥታ አባላቱ የጅላ አባላት ቤተሰብ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናትን ነጥለው የአባ ገዳ ባንዲራ የነበረበት ቦታ ላይ በመሰብሰብ ዛቻና ማስፈራርያ የፈጸሙባቸው መሆኑን፣እንዲሁም ድርጊቱ ከተፈጸመባቸው ሴቶች መካከል አንዲት እናት "ከነ ገዳ ሥርዓታችሁ እናቃጥላችኋለን" ብለው ይዝቱ እንደነበር አስረድተዋል፡፡

የፀጥታ ኃይሎቹ በወቅቱ በቦታው የነበሩ ሁሉንም 39 ወንድ የጅላ አባላትን ከሰበሰቡ በኋላ በእግር ወደ አስፋልት መንገድ (ከአዳማ ወደ መታሃራ የሚወስደው መንገድ) የወሰዷቸው መሆኑን በወቅቱ በቦታው የነበሩ ሴት የተጎጂዎች የቤተሰብ አባላት ይናገራሉ። የኮሚሽኑ የምርመራ ቡድን ካነጋገራቸው ምስክሮች መካከል ወደ አርዳ ጅላው በመምጣት ሟቾችን የያዙ፣ የፖሊስ፣ የሚሊሻ እና የአስተዳደር አባላት መካከል የተወሰኑትን በስም ወይም በመልክ የሚለዩዋቸው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

*አንድ የሟች የጅላ አባል ባለቤት ለኮሚሽኑ ሲያስረዱ፤ "እኛ በሕግ አካላት የተያዙ በመሆናቸው ተመልሰው ይመጣሉ በሚል ተስፋ ሲወሰዱ ብዙም አልተጨነቅንም ነበር፤ነገር ግን የሆነው በተቃራኒው ነው" ብለዋል፡፡*

የጅላ አባላት ወደ አስፋልት መንገድ ከተወሰዱ በኋላ የነበረውን ሁኔታ የተመለከቱ የአይን ምስክሮች በበኩላቸው የሚከተለውን አስረድተዋል፡

የፀጥታ ኃይሎቹ 39 የጅላ አባላቱን *ከተሰበሰቡበት ቦታ ተነስተው ወደ አውራ ጎዳና (ትልቅ አስፋልት መንገድ) እንዲሄዱ አዘዙዋቸው፣ እነሱም ወደ ታዘዙበት አቅጣጫ ሄዱ፣ በዚህ መካከል የከረዩ አባ ገዳ 'እኛ ሕጋዊ ሰዎች ነን፤ ከመንግስት ጋር አብረን ስንሰራ ነበር፣ ለዚህም ከመንግስት አካል የተሰጠን መታወቂያ አለን ለምን እንዲህ ይደረጋል?' ብሎ መታወቂያውን ሲያሳያቸው አንድ የፖሊስ አባል 'መታወቂያህን ይዘህ አብረህ ትሞታለህ' በማለት ቀኝ እጁን መታው፡፡ አስፋልት መንገድ ዳር ሲደርሱ ብዙ የፖሊስ ፓትሮል መኪኖች ቆመው ነበር፤ በተጨማሪም መንገድ ሲሄድ የነበረ አንድ 'ኤፍ.ኤስ.አር አይሱዙ*

*መኪናን አስገድደው አስቆሙ፡፡ የታርጋ ቁጥሩ እንዳይታይ አድርገው ጭቃ ቀብተው የጅላ አባላቱ እንዲሳፈሩ አደረጉ፡፡ በዚሁ መኪና ከዋናው የአስፋልት መንገድ ወጥተው ወደ ውስጥ በመግባት ራቅ ወዳለ ‘ሃምሳ አምስት’ የሚባለው መንገድ አጠገብ ኖቆ በሚባል ቦታ አወረዷቸውና ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጡ ተደረገ፡፡ የመንግስት ባላሥልጣናት ኮብራዎችና የተለያዩ ይዘት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በብዛት ሰዎቹ ወዳሉበት ስፍራ መጡ፡፡ በስፍራው የነበሩ የፀጥታ ኃይሎች እና ሲቪል የለበሱ ሰዎች ጭምር ብዙ የስልክ ንግግሮችን ሲያደርጉ ይታይ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ሟቹ አባገዳ ከድር ሀዋስ ከሚያውቃቸው በቦታው ከተገኙት የመንግስት ባለስልጣናት መካከል አንድ የሚሊሻ ጽ/ቤት ኃላፊን ስም ጠርቶ ስለሁኔታው ቢጠይቀውም፣ ሰውየው አመናጭቆት ከሰደበውና እንደሚገደሉ ከነገረው በኋላ በሆዳቸው እንዲተኙ ተደረገ፡፡ ከመካከላቸው አንዳቸው ቀና በሚሉበት ጊዜ ወደ ታች እየረገጡ ይደበድቧቸው ነበር፡፡ ወደ 12፡00 ሰዓት አካባቢ የጅላ አባላቱን ለሁለት ቡድን ከፈሏቸው፡፡ አባገዳ ከዲር ሀዋስን ጨምሮ 16 ዋና ዋና የጅላ አባላት አንድ ቦታ እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ ቀሪዎቹን 23 የጅላ አባላት ደግሞ ለብቻ በመለየት በመኪና ጭነው ወደ ሌላ ስፍራ ወሰዷቸው”* ካሉ በኋላ የሚከተለውን አክለዋል፡-

> “የ16ቱን ሰዎች ቡድን ወደ ጨቢ አኖሌ ጫካ ከወሰዷቸው በኋላ በረድፍ እንዲተኙ ተደረገ፣ በመጨረሻም የሚገደሉበት ሰዓት እየደረሰ እንደሆነ ተነገራቸው፡፡ ከመሞታቸው በፊት ግን ከመካከላቸው ገንዘብ የያዘ ሰው ካለ እንዲሰጧቸው ጠየቁ፡፡ በዚሁ ጊዜ ለእያንዳንዳቸው ገዳዮች ተመደቡ፡፡ ከ12፡00 ሰዓት በኋላ እንዲገድሏቸውም ትዕዛዝ ተሰጣቸው፡፡”

በዚሁ ሁኔታ የከረዩ አባገዳ ከዲር ሀዋስን ጨምሮ ኡዳ ጫርጨር፣ ቦሩ ፈንታሌ፣ ፈንታሌ ቦሩ፣ ቁምቢ ጉራቻ (ቃሉ ናቸው) ፣ ቦሩ ፈንታሌ፣ ቡላ ፈንታሌ፣ ሮባ ሀዋስ፣ ቦሩ ጎዳና፣ ጂሎ ደዲኦ፣ ቡላ ፈንታሌ፣ ቡልጋ ቦረኡ፣ ጂሎ ዲዶ እና ቦሩ ጂሎ የተባሉ በአጠቃላይ 14 የከረዩ የሚችሌ ገዳ ጅላ አባላት እዛው በሆዳቸው እንደተኙ በጥይት ተመተው መገደላቸውንና ሁለት ሰዎች ደግሞ ከተኙበት ተነስተው ወደ ጫካ በመሮጥ እየተተኮሰባቸው ማምለጣቸውን ገልጸዋል።

በዚሁ እለት ማታ የተያዙ የጅላ አባላት መገደላቸው መረጃ በመሰማቱ፣ የቤተሰብ አባላት እና የሀገር ሽማግሌዎች አስከሬናቸውን ለመውሰድ ግድያው ወደተፈጸመበት ቦታ በማግስቱ አመሩ። ኅዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ግድያው የተፈጸመበት ቦታ ሲደርሱ በቦታው ፖሊሶች ነበሩ፡፡ ፖሊሶቹ ቤተሰብ አስከሬኖቹን እንዳያነሳ በመከልከላቸው ምክንያት ግድያው ከተፈጸመ በኋላ ለበርካታ ሰዓታት አስከሬኖቹ ከሜዳ ላይ መቆየታቸውን፣ይሁንና የሀገር ሽማግሌዎች በተለያየ መንገድ ባደረጉት ጥረትና ድርድር ከ9፡00 ሰዓት በኋላ አስከሬኖቹን ማንሳት መቻሉን የቤተሰብ አባላትና የሀገር ሽማግሌዎች አስረድተዋል፡፡ አስከሬኖቹ ከሜዳ ላይ ሲነሱ ሚኞች ከጀርባ በኩል ወገባቸውና ጭንቅላታቸው ላይ በጥይት ተመተው መገደላቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች የነበሩባቸው መሆኑን አስከሬኖቹን ከሜዳው ላይ በማንሳት የቀበሩ ሰዎች ይናገራሉ።

አስከሬኖቹ ከአንድ ቀን በላይ ሜዳ ላይ በመቆየታቸው የተወሰኑት ፈንድተው የተወሰኑት ደግሞ በዱር እንስሳ መበላታቸውን የቤተሰብ አባላትና፣ አስከሬኖቹን ከሜዳ ላይ ያነሱ የሀገር ሽማግሌዎች ያስረዳሉ። አስከሬኖቹ ከሜዳ ላይ ከተነሱ በኋላ ምንም አይነት ምርመራ ሳይደረግላቸው በማኅበረሰቡ ትብብር ኅዳር 24 ቀን 2014 ዓ.ም. መቱማ ከሚባል ተራራ ዝቅ ብሎ ከዋና አስፋልት አቅራቢያ ባለው ቦታ ላይ በአምስት መቃብሮች የተቀበሩ ሲሆን፣ የምርመራ ቡድኑ የቀብር ቦታውን ተመልክቷል።



**1** የተገደሉ የጅላ አባላት የተቀበሩበት ቦታ

ኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ተይዘው ከተወሰዱት 39 የጅላ አባላት መካከል 23ቱ ወዴት እንደተወሰዱ ቤተሰብ ለቀናት አያውቅም ነበር፡፡ ይሁንና ከሁለት ሳምንታት በኋላ ተይዘው ከተወሰዱት መካከል አንዱ የነበረው ጅሎ ቦረዩ የተባለ የጅላ አባል ሕይወቱ አልፎ አስከሬኑ በሞጆ ከተማ ከሚገኝ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ካምፕ ለቤተሰብ ተሰጥቷል፡፡ በአስክሬኑ ጭንቅላት ላይ የመፈንከት፣ በተለያዩ የሰውነቱ ክፍሎች ላይ ቁስል እና የድብደባ ምልክቶች ይታዩ እንደነበረ አስክሬኑን የተቀበሉ የቤተሰብ አባላት ገልጸዋል፡፡

በክስተቱ በገዳ ሥርዓቱ ዋና ዋና የኃላፊነት ቦታ ላይ የነበሩ ግለሰቦች በመገደላቸውና፤ ቀሪዎቹም በመታሰራቸው በቦታው ሲከናወን የነበረ የገዳ ሥርዓት የተቋረጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። አንድ የሀገር ሽማግሌ ስለ ሁኔታው ሲያስረዱ *“የከረዩ አባገዳ እና አርዳ ጅላ የተከበረ ስፍራ በመሆኑ እንዲህ አይነት ድርጊት ከዚህ በፊት በነበሩት ጊዜያት ያልተለመደና፣ በከረዩ ማኅበረሰብ ህልውና ላይ ከፍተኛ አደጋና ስጋት የደቀነ ነው”* በማለት ገልጸዋል፡፡

ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የሟቾች ቤተሰቦች፣ የአይን ምስክሮች እና የሀገር ሽማግሌዎች ከጥቃቱ በፊት የከረዩ ማኅበረሰብ ከመንግስት ጋር ጥሩ ግንኙነት የነበረው መሆኑን ጠቅሰው፣ መንግስት በሰሜን የሀገሪቷ ክፍል እየወሰደ ያለውን እርምጃ በመደገፍ ጭምር ሰልፎች ሲደረጉ እንደነበር አስረድተዋል፡፡ ይሁንና ጥቃቱ ከተፈጸመ በኋላ የኮሚሽኑ መርማሪዎች በቦታው እስከተገኙበት ጊዜ ድረስ መንግስት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥም ሆነ ማኅበረሰቡን በማወያየት ለማረጋጋትና ለማጽናናት ጥረት አለመደረጉንና፤ *“ይልቁንም የመንግስት የፀጥታ አካላት በግልጽ የፈጸሙትን ተግባር ለመደበቅ ጥረት ሲደረግ መመልከታቸው”*እንዳሳዘናቸው የሟቾች ቤተሰቦች ገልጸዋል፡፡

## የመንግስት አካላት ምላሽ

ኮሚሽኑ ከአካባቢው መስተዳድር፣ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደርና የፀጥታ ጽ/ቤቶች ስለ ጉዳዩ መረጃ አሰባስቧል፣ ምላሽ ተቀብሏል፡፡

የኮሚሽኑ የምርመራ ቡድን በቦታው በነበረበት ወቅት በፈንታሌ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት በስራ ላይ የነበሩ ፖሊሶች “በኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በወረዳው ሀሮ ቀርሳ ቀበሌ አካባቢ በታጣቂዎች ከተገደሉ በኋላ አባገዳዎች በኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. የፈንታሌ ወረዳ ድንበር አካባቢ በቦሰት ወረዳ ውስጥ ተገድለዋል” የሚል መረጃ ብቻ እንዳላቸውና ጉዳዩን ለማጣራት እና ምላሽ ለመስጠት ሥልጣን ያለው አካል የቦሰት ወረዳ ፖሊስ መሆኑን ገልጸዋል።

የቦሰት ወረዳ አስተዳደር በበኩሉ ችግሩ የተፈጠረው በፈንታሌ ወረዳ ውስጥ በመሆኑ በቀጥታ ወረዳውን እንደማይመለከትና የወረዳውን ፖሊስ ማነጋገር የተሻለ እንደሚሆን አስረድቷል።  የቦሰት ወረዳ ፖሊስን ለማግኘት ተደጋጋሚ ጥረት የተደረገ ቢሆንም “የወረዳው የፖሊስ አመራር በልዩ የፀጥታ ማስከበር ስራ ላይ መሆናቸው” በመገለጹ ምላሽ የሚሰጥ ኃላፊ ማግኘት አልተቻለም።

የምሥራቅ ሸዋ ዞን አስተዳደር “ከከረዩ አባገዳዎች ጋር በሰላም ዙሪያ አብረው ሲሰሩ” እንደነበር ጠቅሰው “የተፈጸመው ግድያ መንግስትና ሕዝብን ለማራራቅ የተፈጸመ የጠላት/“ኦነግ ሸኔ” ሴራ” መሆኑን  ገልጸዋል፡፡ አክለውም *“ሟቹ የከረዩ አባ ገዳ ከዚህ በፊት በጠላት ዛቻ ይፈጸምበት እንደነበር በተደጋጋሚ ሲገልጽልን ነበር”* ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በአከባቢው የተፈጠረውን ክስተት ለማጣራት ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ውይይቶችን ማድረጋቸውንና “ለኦፕሬሽን ስራ ተሰማርተው ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ የፀጥታ አባላት በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው” መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢሰመኮ ታኅሣሥ 22 ቀን 2014 ዓ.ም. ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በደብዳቤ ቁጥር *ሰመኮ/2.1/42/2014* በላከው ደብዳቤ በምርመራው ግኝቶች ላይ ምላሽ እንዲሰጡ የጠየቀ ቢሆንም፣ ሁለቱም መስሪያ ቤቶች ሪፖርቱ ይፋ እስከተደረገበት እለት ድረስ ምላሽ አልሰጡም። በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ምላሻቸውን ማካተት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩል ኅዳር 24 ቀን 2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮሙኒኬሽን ቢሮ ባወጣው መግለጫ “አባገዳ ከዲር ሀዋስ የከረዩ ሕዝብ ለመንግስት ድጋፍ ሰልፍ መውጣቱን ተከትሎ ሕዝብ የምታነሳሳብን አንተ ነህ በሚል ቂም በኦነግ ሸኔ መገደሉን” ገልጿል፡፡ በተመሳሳይ የኦሮሚያ ብልጽግና ፓርቲ ታኅሣሥ 20 ቀን 2014 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ በተራ ቁጥር 5 ስር “…የከረዩ አባገዳዎች ግድያ በተለያየ መልኩ እየተነሳ ነው፡፡ ይሁንና መቼም ቢሆን እንደዚህ አይነት ጉዳይ በግለሰቦች ደረጃ የሚገለጽ ጥፋት ሊሆን ይችላል እንጂ ሕዝብ በራሱ የመሰረተው መንግስትን አይገልጽም…” በማለት ያስቀምጣል፡፡

## ምክረ ሃሳብ

በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 14 እና 15 እንዲሁም ኢትዮጵያ ፈርማ ባጸደቀችው የዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖሊቲካ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 6(1) መሰረት፣ ማንኛውም ሰው በከባድ ወንጀል በፍርድ ቤት ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር በዘፈቀደ ሕይወቱን ሊነጠቅ የማይገባ መሆኑንና መንግስት የሰዎችን በሕይወት የመኖር መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋሉ፡፡

ኮሚሽኑ በዚህ ጉዳይ በሰበሰባቸውና ባገናዘባቸው ማስረጃዎች መሰረት 14 የከረዩ የሚችሌ ገዳ አባላት ከላይ በተገለጸው ቦታና ጊዜ በመንግስት የፀጥታ አካላት በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ በግዳጅ ወደ ጫካ ቦታ ተወስደውና የፀጥታና የአካባቢ አስተዳደር ሰዎች ባሉበት ጭካኔ በተሞላው ሁኔታ በጥይት ተመተው የተገደሉ መሆኑን፤ ይህም ከሕግ ውጭ የተፈጸመ ግድያ (extra judicial killing) ስለመሆኑ በምክንያታዊ ሁኔታ አሳማኝ (reasonable ground to believe) ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ በግዳጅ ከተወሰዱት 23 የጅላ አባላት መካከል አንድ ሰው ሞጆ ከተማ በሚገኝ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ካምፕ ውስጥ በቁጥጥር ስር እያለ  ሕይወቱ አልፎ  ያለምንም ምርመራ አስከሬኑን ቤተሰቦቹ

እንዲወስዱና እንዲቀበር መደረጉ ከዚሁ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ተጨማሪ ከሕግ ውጭ የተፈጸመ ግድያ (extra judicial killing) መኖሩን በምክንያታዊ ሁኔታ አሳማኝ (reasonable ground to believe) ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ስለሆነም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የሰዎችን ሰብአዊ መብቶች ከማክበርና ከማስከበር አንጻር ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት፡-

- በከረዩ የሚችሌ ገዳ አባላት ላይ ድብደባ እና ከሕግ ውጪ የሆነ ግድያ የፈጸሙና ያስፈጸሙ የአስተዳደርና የፀጥታ አባላት ተገቢው የወንጀል ምርመራ ተደርጎባቸው በሕግ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ፣

- ለሟቾች ቤተሰቦች እና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ለደረሰባቸው ጉዳት ተገቢ የሆነ ካሳ እንዲከፈል፣

- በስራ ላይ እያሉ የተገደሉና የአካል ጉዳት የደረሰባቸው የፖሊስ አባላት ላይ የወንጀል ጥቃት የፈጸሙ ሰዎችን በሚመለከትም ተገቢውን የወንጀል ምርመራ በማድረግ በሕግ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ያሳስባል፡፡